# መመሪያ/ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ምንጮች፡-** ABC፣ ABC-RA፣ BMA፣ IFA፣ IFA-RA፣ IIB፣ IIB-RA

**ኃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት፡-** Chief of Teaching, Learning, and Schools

## አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ ፕሮግራም

I. **ዓላማ**

የሜሪላንድ ህግ በሚደነግገው እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በፀደቀው መሠረት ለሁሉም ተማሪዎች አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ ፕሮግራምን ተግባራዊ የማድረግ ዝርዝር ለመንደፍ

II. **የበፊት ታሪክ ወይም ዳራ**

የሜሪላንድ ስቴት የጤና ትምህርት ከሪኩለም ተማሪዎች ጤንነትን ለመጠበቅ እና ለጤንነታቸው አስጊ ነገሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚረዳቸው ጤናማ ስነምግባር እንዲኖራቸው ደረጃ የጠበቀ ስድስት ፍሬነገሮችን ያካተተ ነው። የጥናት ክፍሎቹ ፍሬነገሮች ስለ አእምሮ እና ስሜታዊ ጤንነት፣ የአደንዛዥ እፅ መጥፎ አጠቃቀምን ስለመከላከል፣ ስለቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ የወሲብ ፍላጎት (FLHS)፣ ስለ ሠላምና ደህንነት እና ብጥብጥንና ረብሻን መከላከል፣ ስለ ጤናማ አመጋገብ፣ እና ስለ በሽታ መከላከል እና ቁጥጥር የመሣሠሉትን የሚዳስሱ ናቸው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሜሪላንድ ሕግ ጋር የተጣጣመ፣ እና በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ከተነደፈዉ ስርዓተ-ትምህርት ጋር የተጣጣመ አጠቃላይ የጤና ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ያቀርባል።

III. **የቅደም-ተከተል ሥርአቶች**

A. የስርዓተ-ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ

በ MCPS ደንብ IFA-RA በተዘረዘሩት ቅደም ተከተሎች መሠረት፣ ሥርዓተ-ትምህርት፣ የሥርዓተ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴዎች (CACs) ለእያንዳንዱ ዘርፍ/ዲሲፐሊን ይዘት-ተኮር የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ እንዲወያዩ፣ እና እንዲያማክሩ የተመሰረቱ ናቸዉ።

CAC ለአጠቃላይ የጤና ትምህርት ከባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ተወካዮችን ያቀፈና የ MCPS ሶሺዮኢኮኖሚክ/ማህበራዊ፣ ቋንቋ፣ እና ባህላዊ ብዙአነትን ይወክላል። CAC ለአጠቃላይ የጤና ትምህርት ስለ MCPS አጠቃላይ የጤና ትምህርት የትምህርት አሰጣጥ መርሃግብር፣ አዘገጃጀት፣ አተገባበር፣ ክትትል፣ እና ክለሳ ግብረ መልስ ለመስጠት ግምገማ እና ዉይይት ያካሂዳል።

8. የማስተማሪያ ማቴሪያሎች

ለትምህርት ፕሮግራሙ መጠቀሚያ የሚሆኑ መጻሕፍት፣ ቪድኦዎች፣ እና ሌሎችም የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች የሚፀድቁት በቦርድ ፖሊሲ "Board Policy IIB" እና መገምገምና መምረጥ-Evaluation and

Selection እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ "MCPS Regulation IIB-RA" የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና የቤተመጻህፍት መጽሐፎችን ስለመገምገም እና አመራረጥ-"Evaluation and Selection of Instructional Materials and Library Books" መሠረት በሚከናወን ሂደት ነው።

C. የሙያ ማዳበር ትምህርት

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት –

1. ብቃት ያላቸው አስተማሪዎችን ለመደገፍ መመሪያዎችን እና የአሠራር ስልቶችን ማዘጋጀት፣ እና

2. የሜሪላንድ ሕግ በሚደነግገው መሠረት ለጤና ትምህርት ኃላፊነት ያላቸውን የ MCPS አስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ እና ሱፐርቫይዘሮችን ለማሰልጠን ዝግጅት የተደረገባቸዉ እና ቀጣይነት ያላቸዉን ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ እና በየዓመቱ በጤና ትምህርት ረገድ ዕውቀትን፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን፣ እና ስልቶችን/ዘዴዎችን ዘመናዊ ማድረግ።

D. ገመና መጠበቅ

የታሰቡት/የተጠቆሙት ማናቸውም እንቅስቃሴዎች የተማሪን ወይም የቤተሰብን ግላዊ ገመና የማይጥሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የ MCPS አጠቃላይ የጤና ትምህርት የትምህርት መርሐግብር በጥንቃቄ ይገመገማል። ዉይይቶች በተማሪ ቤተሰብ ውስጥ ግላዊ ግንኙነቶችን ለማክበር እና የቤተሰብን ግላዊነት/ፕራይቬሲ እንዳይጥሱ ለማበረታታት ነዉ።

E. ስለ ቤተሰብ ህይወትና ሰብአዊ የወሲብ ፍላጎት የጥናት ክፍል - "FLHS Unit of Study"

1. በዚህ ምዕራፍ ላይ ባለው መስፈርት እያንዳንዱ ተማሪ በአጠቃላይ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ እድል ይኖረዋል/ይኖራታል።

2. የሜሪላንድ FLHS ትምህርት ችሎታን፣ የጾታ ዝንባሌን፣ የጾታ ማንነትን፣ እና የጾታ አገላለጽን ሳይመለከት ሁሉንም ተማሪዎች ይወክላል።

3. "consent" መስማማት ስለሚለው እና የግል ገመና ገደብን ስለማክበር ትርጉም ከሪኩለሙ ትምህርት በሚሰጥበት በሁሉም የክፍል ደረጃ ዕድሜን የሚመጥን ትምህርት መሆን እንዳለበት ስለ FLHS ከሪኩለም የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል። በሜሪላንድ ህግ ትርጉም መሠረት "consent" ማለት የሚመለከታቸው ሁሉ በእርስበርስ ግንኙነቶች መሃል፣ የግል ገመና ገደብን ጨምሮ ስለ እያንዳንዱ አካላዊ ንክኪ የማያሻማ ግልጽ የሆነ እና በፈቃደኝነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ስምምነት ይሆናል [1]።

4. ለወላጅ/ሞግዚት ማሳወቂያ

a) ስለ FLHS ጥናት ትምህርትን በሚመለከት ለወላጆች/ለሞግዚቶች በጽሑፍ እንዲያውቁት ይደረጋል።

b) እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ስለ FLHS ትምህርት ከአስተማሪዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን የሚመለከቱበት እድል ይሰጣቸዋል። የመረጃ ልውውጥ ስብሰባ መሣተፍ ለማይችሉ

[1] በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ (Annotated Code of Maryland)፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-445

ወላጆች/ሞግዚቶች፣ በጥናት ክፍሉ (ዩኒት) ለማስተማሪያ መጠቀሚያ ቁሳቁሶችን በመማሪያ ክፍሎች ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት ወላጆች/ሞግዚቶች ለመመልከት እንዲችሉ ትምህርት ቤቱ የተለያዩ እድሎችን ያዘጋጃል።

c) ስለ FLHS ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት እንዳይማሩ ከወላጅ/ከሞግዚት በጽሑፍ ጥያቄ ከቀረበ ተማሪዎች እንዳይሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይችላል። ከክትትል ነፃ ለተደረጉ/ለተፈቀደላቸዉ ተማሪዎች፣ ትምህርት ቤቱ በጤና ትምህርት አማራጭ የመማር እንቅስቃሴዎችን ይሰጣል።

2. ስለ FLHS የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች

የ FLHS ቁሳቁሶችን በትምህርት ቤቱ ማናቸውም ሌሎች የማስተማሪያ ፕሮግራም አይጠቀሙበትም።

3. የ FLHS አስተማሪ መምረጥ እና ስልጠና

በአጠቃላይ ከመምህር ዝግጅት በተጨማሪ፣ ከ FLHS ጋር የተገናኙ ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶችን በሚያስተምሩበት ወቅት፣ ከማስተማሪያ ቁሳቁሶች ጋር የሚመጣጠን ጥልቀት እና የሚወስደውን ያክል ጊዜ በተመለከተ መምህራን በይዘት እና በትምህርት አቀራረብ ስልት ተጨማሪ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተጨማሪ ዝግጅቱ በኮሌጅ ኮርሶች፣ በአካባቢ የአገልግሎት ፕሮግራሞች፣ እና/ወይም በሜሪላንድ አውደጥናቶች አማካይነት ይሰጣሉ።

E. በትምህርት ቤት ስለ FLHS ማስተማር

ርዕሰ መምህር/ት ይህንን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች፦

1. ስለ FLHS ትምህርት ለወላጅ/ሞግዚት የመረጃ ልውውጥ ስብሰባ እቅድ ለማዘጋጀት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአካባቢ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ቡድን ይመሠረታል።

a) የዕቅድ ቡድኑ ወላጆችን/ሞግዚቶችን፣ መምህራንን፣ የአካባቢ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችን፣ እና አግባብነት ካለዉ፣ የተማሪ ተወካዮችን ያካትታል።

b) የኮርስ አቅርቦቶች፣ ይዘታቸው፣ እና አገልግሎት ላይ የሚዉሉ ትምህርታዊ ማቴሪያሎችን በተመለከተ የተማሪ አስተያየቶች እና ምክረሀሳቦች አግባብነት ሲኖራቸዉ፣ በፋከልቲዉ እና በአስተዳዳር ይፈቀዳል እናም በንቃት ይጠየቃል/ይፈለጋል።

c) የዕቅድ ቡድኑ ተግባራት/እንቅስቃሴዎች በየዓመቱ ክትትል ይደረግባቸዋል። ስለ ቤተሰብ ህይወት እና ስብአዊ ወሲብ (FLHS) ልምድ መለዋወጫቅ ስብሰባ ዓመታዊ ሪፖርት፣ MCPS Forms 345-30ag (ለኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች)፣ 345-30bg (ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች-ሚድል ስኩልስ)፣ እና 345-30cg (ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በአግባቡ የሚሞላ ሲሆን በእቅድ አዘጋጁ ቡድን ስለተካሄደው የ FLHS ፕሮግራም የግምገማ ተግባሮችን የተጠቃለለ ሪፖርት ያካትታል።

2. ትምህርቱ በዲፕሎማ የተያዙ እና ከዲፕሎማ ጋር ባልተያያዙ ተማሪዎች የሜሪላንድ ሕግ በሚጠይቀዉ በቦርድ በሚጸድቅ ስርዓተትምህርት ማዕቀፍ መሰረት ነዉ።

3. መምህራን በ MCPS- ተቀባይነት ያገኙ ማቴሪያሎችን እና የካውንቲ ወይም የስቴት ትምህርታዊ ሪሶርሶችን እና ማቴሪያሎችን ብቻ ይጠቀማሉ።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, Education Article, §§7-401, 7-410, 7-411, 7-411.1, 7-413, and 7-445; Code of Maryland Regulations §13A.04.18, Program in Comprehensive Health Education

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** የበፊት ደንብ ቁ. 360-1፣ ጃኑወሪ 24/1978 (የማውጫ መረጃው ተሻሽሏል)፣ ኦገስት 1984 ክለሳ ተደረገ፣ ዲሰምበር 1986 ክለሳ ተደርጓል፣ ዲሰምበር 18/1992 ክለሳ ተደርጓል፣ ጁን 14/2004 ተከልሷል፣ ሴፐተምበር 20/2005 ተከልሷል፣ ማርች 21/2016 ክለሳ ተደጓል፣ ጁላይ 5/2018 ክለሳ ተደርጓል፣ ሴፐተምበር 2/2020 ተሻሽሏል።